# ለጽንስ ማስወረድ ሂደት - ቀዶ ጥገና

## ሆነ ተብሎ እያወቁ ጽንሱን ለማቋረጥ ከፈለጉ በቀዶ ጥገና ጽንስን ማስወረድ አንደኛው መንገድ ነው

የመጀመሪያው እርምጃ ምክር ለማግኘት ቀጠሮ ማቀናጀት ነው። በዚህ የምክር ጊዜ ላይ ሀኪም የሚያደገው:

- ይህ የአሠራር ሂደት ለርስዎ የሚስማማ ከሆነ ማሳወቅ
- በቀዶ ጥገና ጽንስን ስለማስወገድ የአሠራር ሂደቱን መግለጽ
- የአልትራሳውንድ እና የደም ምርመራን እንደአስፈላጊነቱ ማቀናጀት
- በዚህ የሚቀጥሉበት ከሆነ በስምምነት መስጫ ቅጽ ላይ እንዲፈርሙ መስጠት
- ጽንሱን ለማስወረድ ቅንጅት ማውጣት ይሆናል።

በአንዳንድ ክሊኒኮች ላይ ምክሩ በሚካሄድበት ተመሳሳይ ቀን የጽንስ ማስወረድ ሂደት ሲካሄድ፤ በሌሎች ክሊኒኮች ላይ ደግሞ በሌላ ቀን ይደረጋል።

## ለቀዶ ጥገና ጽንስ ማስወረድ ስለመዘጋጀት

- ቀዶ ጥገና ከመካሄዱ በፊት ለስድስት ሰዓታት በፊት ጀምሮ ሲጋራ አያጭሱ፤ አምግብ አይብሉ ወይም ውሃ አይጠጡ፡ል። ይህ የማደንዘዣ መድሃኒት/anaesthetic በሚወስዱበት ጊዜ ለርስዎ ደህንነት ሲባል ነው። .
- በክሊኒኩ ውስጥ ለጥቂት ሰዓታት ለመቆየት ማቀድ ነው።
- ማምጣት ያለብዎት:
  - ንጽህና መጠበቂያዎች
  - ወደዚህ የተላኩበትን ደብዳቤ (አስፈላጊ ከሆነ)
  - የርስዎን መዲኬር ካርድ/Medicare card
  - የርስዎን ሀልዝ ኬር ካርድ/health care card (ጠቃሚ ከሆነ), እንዲሁም
  - ክሊኒኩ የጠየቀው ማንኛውም ነገር ይሆናል።
- ወደ ቤትዎ የሚወስድዎ ሌላ ሰው ማዘጋጀት።

## በቀዶ ጥገና ጽንስ ለማስወረድ ማደንዘዣ

እንደ ክሊኒኩ ውሳኔ ለአሠራር ሂደት የማደንዘዣ መድሃኒት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:

- አጠቃላይ ማደንዘዣ – የአሠራር ሂደቱ በሚካሄድበት ጊዜ አይነቁም
- ናይትረስ ኦክሳይድ ጋዝ/nitrous oxide gas – 'በብርሃን ደንዝዞ መተኛት/twilight sleep' (ይነቃሉ ነገር ግን በመደንዘዝ ረጋ እንዲሉ ያደርጋል)
- የአካባቢ ማደንዘዣ – አካባቢውን ለማደንዘዝ በርስዎ ማህጸን ጫፍ ውስጥ የሚወጋ የማደንዘዣ መርፌ ሲሆን፤ ወይም
- የአካባቢ ማደንዘዣ ከማረጋጊያ ጋር ይሆናል።

## በቀዶ ጥገና ጽንስ ማስወረድ አሠራር ሂደት

አብዛኛው የቀዶ ጥገና ጽንስ የማስወረድ ሂደት የሚከናወነው 'በመምጠጥ (ባዶ) በማድረግ ሲሆን በአብዛኛው ከ15 ደቂቃዎች በታች ይወስዳል።

የአሠራ ሂደቱ እንደሚከተለው ይሆናል:

- የርስዎ ማህጸን ጫፍ ቀስ በቀስ ይሰፋል።
- ከዚያም ቀጭን ቱቦ በማህጸንዎ ውስጥ ይገባል።
- ቀስ አድርጎ በመምጠጥ ጽንሱ እንዲወገድ ይደረጋል።

VICTORIA State Government | Health and Human Services

- ኩሬት የሚባል መሳሪያ በመጠቀም በማህጸን ውስጥ ጽንስ ባዶ ስለመሆኑ ማጣራት።

## በቀዶ ጥገና ጽንስን ካስወረዱ በኋላ

ኢንፌክሽን ብክለትን ለመቀነስ፤ ሂደቱን ከወሰዱ ከሁለት ሳምንታት በኋላ (ወይም ደም ከቆመ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ):

- በገንዳ ውስጥ ከመታጠብ ፋንታ በሻወር መታጠብ
- ወሲባዊ ግንኙነትን ማስወገድ
- መዋኘትን ማስወገድ
- ታምፒን ከመጠቀም ፋንታ የንጽህና ፓዶችን መጠቀም።

## ጽንሱን ካስወረዱ በኋላ የህክምና ምክር ሲያስፈልግ

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ተከታታይና ቀጣይ የሆነ ቀጠሮ ከሀኪምዎ ጋር ይኖርዎታል።

ከዚህ በታች ያሉት ከተከሰተ ወዲያውኑ ወደ ክሊኒክ፤ አጠቃላይ ሀኪም/GP ወይም ወደ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል ወዲያውኑ መሄድ ያስፈልጋል:

- የሚፈስዎ ደም ከባድ ሲሆን
- ትኩሳት ከተፈጠረብዎ
- በጣም ሃይለኛ የጡንቻ መሸምቀቅ ወይም የሆድ እቃ (ከርስ) ህመም ካጋጠምዎት ይሆናል።

## በቀዶ ጥገና ጽንስ ማስወረድ የሚከሰት የጎንዮሽ ጉዳትና የጤና ውስብስብ

በቀዶ ጥገና ማስወረድ የጤና ውስብስቦች መከሰት በጣም አነስተኛ ሲሆን ከመቶ እጅ ሶስት ይሆናል። በመጀመሪያ ትራይሚስተር ጽንስ ማስወረድ ሲካሄድ፤ በጣም ትንሽ ውስብስብ ብቻ ይከሰታል።

**በመድሃኒት ጽንስ ማስወረድ ላይ ከባድ አዲሽ በሽታ ችግር መፈጠር ያልተለመደ ሲሆን ነገር ግን ከዚህ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል:**

| የጤና ውስብስቦች | ምልክቶች ወይም የጎንዮሽ ጉዳቶች | ምን መደረግ እንዳለበት |
|---|---|---|
| **የደም ስር መበጠስ/ Haemorrhage** (በጣም ከባድ መድማት) ማስወረቅዱ ሙሉ በሙሉ እንዳላለቀ ሊያሳይ ይችላል | • ከሁለት ሰዓታት በላይ የሚሆን ከሁለት ትላልቅ ሞዴስ በላይ በሰዓት ውስጥ በደም መሞላት<br>• ትንሽ የሎሚ መጠን ያለው የደም መርጋት ማስተላለፍ<br>• የድካም መንፈስ ወይም እራስን መሳት ይሆናል። | • በአስቸኳይ ለህክምና ትኩረት ይጠይቁ<br>• ለአምቡላንስ በስልክ 000 መደወል ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል መሄድ (እራስዎ መኪና አይንዱ፤ ሌላ ሰው እንዲወስድዎ ያቀናጁ)<br>• ሰክሽን ኩሬትጅ በሚባል መሳሪያ ማህጸንን ሊያክም ይችላል።<br>• የሌላ ሰው ደም ልገሳ ያስፈልግ (ይህ በጣም አነስተኛ) ይሆናል። |
| **ኢንፌክሽን ብክለት** | ሊከሰት የሚችል:<br>• የጡንቻ መኮማተር ወይም የሆድ እቃ (የከርስ) ህመም -<br>• ያልተለመደ በብልት ላይ ፈሳሽ መውጣት<br>• ትኩሳት<br>• ከባድ የደም መፍሰስ<br>• ድካም<br>• ተቅማጥ<br>• ማስታወክ ይሆናል። | • በአስቸኳይ ለህክምና ትኩረት ይጠይቁ<br>• የርስዎን ክሊኒክ፤ አጠቃላይ ሀኪም/GP ማየት ወይም አንቲባዮቲክ ህክምና ለማግኘት ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል የድንገተኛ ክፍል መሄድ። |
| **የማህጸን መጎዳት**<br>ይህ መከሰቱማ በጣም አነስተኛ ነው ምክንያቱም የቀዶ ጥገና ማስወረድ ሥራ የሚካሄደው ልምድ ባለቸው የቀዶ ጥገና ባለሙያዎች ስለሆነ | • በቀዶ ጥገና ሀኪም ይታወቃል። | • ይህ በቀዶ ጥገና ባለሙያው ስለሚታወቅ ወዲያውኑ ህክምና ይደረጋል |

| የጤና ውስብስቦች | ምልክቶች ወይም የጎንዮሽ ጉዳቶች | ምን መደረግ እንዳለበት |
|---|---|---|
| **ለማህጸን ጫፍ መጉዳት ወይም ስለማዳከም**<br><br>የዚህ ክስተት በጣም አነስተኛ ሲሆን ምክንያቱም የጽንስ ማስወረድ ሥራ የሚካሄደው ልምድ ባላቸው የቀዶ ጥገና ባለሙያዎች ስለሆነ | • በወደፊት እርግዝና ላይ ይህ ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል። | • ለወደፊት እርግዝና ጊዜ በርስዎ የማህጸን ባለሙያ በኩል ምክር ይቀርባል |

## የበለጠ መረጃ

ይህ የመረጃ ጽሁፍ በ Health Translations Directory ካሉት ሶስት ጽሁፎች ውስጥ አንዱ ነው። እባክዎ የሚከተሉትንም ይመልከቱ:

- የጽንስ ማስወረድ አሠራር ሂደት - በመድሃኒት
- ጽንስ ማስወረድ

በቪክቶሪያ መንግሥት ሥልጣን ያገኘና የታተመ፤ አድራሻ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፤ January 2019.
በድረገጽ <http://healthtranslations.vic.gov.au/> ላይ ቀርቧል።